

fka CHILDREN'S SERVICES INC

# በቅድመ ልጅነት መቼት ውስጥ በጨዋታ መማር

AMHARIC

## ጨዋታ ምንድን ነው?

በዓለም ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ልጆች ትርጉም ባላቸው ጨዋታን መሰረት ያደረጉ ልምዶች ውስጥ ሲሳተፉ እንደሚማሩ እና እንደሚዳብሩ አሳይተዋል።

*"“ጨዋታ ሰፋ ያሉ የልጆችን አእምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ እና የፈጠራ ችሎታዎችን ለማነቃቃት እና ለማዋሃድ አስፈላጊ ነው። ውጤታማ የሆኑ የቅድመ ልጅነት ተግባሮች ከልጆች ጋር ዘላቂ እና የጋራ መስተጋብርን ለመደገፍ የተዋሃዱ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። በጨዋታ እና በሌሎች እድሎች ውስጥ ልጆች ስለ ማህበራዊ እና ተፈጥሯዊው አለም ፣ ሰዎቹ፣ ቦታዎች፣ እቃዎች እና በየቀኑ ለሚገጥሟቸው ልምዶች ትርጉም መስጠትን እና ሃሳቦችን መገንባት ይማራሉ።”*

- VEYLDF, 2016, pg. 14

ጨዋታ፣ ወደ ልጆችዎ በተፈጥሮ የሚመጣ ሲሆን የመማራቸው እና የመዳበራቸው አስፈላጊ አካል ነው። ጨዋታ፣ ልጅዎ የዓለማቸውን ትርጉም እንዲሰጡ እና ጠንካራ የማንነት ስሜት እንደያዳብሩ ይረዳቸዋል። በጨዋታ ውስጥ ልጅዎ ራሱን/ራሷን ማየት፣ ማስመሰል፣ መፍጠር፣ ማሰስ፣ መመርመር፣ መገናኘት፣ መጠየቅ፣ ማውራት፣ ማዳመጥ፣ ማሰብ፣ መዳሰስ፣ መንካት እና ማሽተት ይችላል/ትችላለች። ጨዋታ፣ መደራደርን ፣ ችግር መፍታትን፣ ሃላፊነት መውሰድን፣ አዳዲስ ነገሮችን መሞከር እና ነገሮች እንዴት እንደሚሰሩ ማየትን ያካትታል። ልጅዎ ስለራሳቸው እና ስለሌሎች ይማራሉ፣ የጨዋታ ህጎችን ይማራሉ፣ ጓደኛ ያፈራሉ፣ ግንኙነቶችን ያዳብራሉ እንዲሁም በዙሪያቸው ያሉትን አስተማሪዎች እና ሌሎች ልጆችን ጭምር ያምናሉ።

ልጆች አንዳንዴ ብቻቸውን ፣ ከሌላ አንድ ወይም ሁለት ልጆች ጋር እና በትንሽ ወይም ትልቅ የልጆች ቡድኖች ውስጥ ይጫወታሉ። ጨዋታ በጩኸት የተሞላ ወይም ፀጥ ያለ፣ ቀዝቀዝ ያለ ወይም ንቁ ሊሆን ይችላል።

*“ያልተቆራረጡ የጨዋታ ጊዜያቶች ለልጆች በአይነት የበለጸጉ ክፍት የሆኑ ቁሳቁሶችን እና ግብአቶችን በመጠቀም ለመፈልሰፍ፣ ለመርመር እና ለማወቅ ጊዜ ይሰጣሉ። ”*

- VEYLDF, 2016, pg. 21

## በጨዋታ ውስጥ መማር

መምህራን እና አስተማሪዎች አገልግሎቱን የሚከታተል የእያንዳንዱን ልጅ የግል ጥቅሞች እና ፍላጎቶች ለሟሟላት ፕሮግራም ያቅዳሉ። ይህን የሚያደርጉት ልጆች በቤት ውስጥ እና በውጭ ቦታዎች ውሳጥ በነፃነት መንቀሳቀስ በሚችሉበት ክፍት የመማሪያ አካባቢ ውስጥ ሰፋ ያሉ በጨዋታ ላይ የተመሰረቱ ልምዶችን በማቅረብ ነው።

አንዳንድ እንደ ሙዚቃ፣ ታሪኮች እና ውይይት ያሉ የተመሩ መደበኛ እንቅስቃሴዎች ይኖራሉ። ለቀኑ አብዛኛው ክፍል ፣ ልጆች የት እንደሚጫወቱ፣ ከማን ጋር እንደሚጫወቱ እና በአንድ የተወሰነ የጨዋታ እንቅስቃሴ ውስጥ ምን ያክል ጊዜ እንደሚያሳልፉ በራሳቸው ውሳኔ ይደርጋሉ። ልጆች እርዳታ በሚፈልጉበት ጊዜ አስተማሪዎች ድጋፍ እና መመሪያ ይሰጣሉ።

አስተማሪዎች ልጆች የመማር ፍቅርን እንዲያዳብሩ፣ ፣ የማወቅ ጉጉት እንዲኖራቸው፣ ጠያቂ እንዲሆኑ እና በዓለማቸው እና በሚያገኟቸው ሰዎች ላይ ፍላጎት እንዲኖራቸው ለመርዳት የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን ይጠቀማሉ። ጨዋታው ላይ አመራር መስጠት፣ ጨዋታውን መምራት ወይም በራስ የሚመሩ ጨዋታዎች ላይ ልጆቹን መመልከት ይችላሉ።

## ልጆች በጨዋታ ጊዜ ምን እየተማሩ ነው?

ጨዋታ፣ ልጆች እንዲናገሩ እና ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ፣ ቃላትን እና ቋንቋን፣ማንበብና መጻፍን፣ የቁጥር እና ማህበራዊ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ እና እንዲለማመዱ እድል ይሰጣል። በጨዋታ ውስጥ ልጆች እንዴት መግባባት እና ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘት እንደሚችሉ ይማራሉ።

እንዲሁም ልጆች ያዩትን ነገር ለመተግበር ምናባቸውን ይጠቀማሉ፣ ለምሳሌ፦

- ምግብ እንደሚያዘጋጁ ማስመሰል
- ለህጻን እንክብካቤ ማድረግ
- የእሳት አደጋ ተከላካይ፣ ዶክተር ወይም ባለሱቅ መሆን።

ይህም ልጆች ዓለማቸው እና ማህበረሰባቸውን እንዲረዱት እና ትርጉም እንዲሰጡት ለመማር ይረዳል።

*"ድራማዊ ይዘት ያለው ጨዋታ፣ የዓለማቀፋዊ ማህበረሰቦች አባል መሆንን ጨምሮ የተለያዩ ማንነቶችን እና አመለካከቶችን ለማሰስ አስፈላጊ ነው። ልጆች በግለሰቦች እና ቡድኖች መካከል የሚኖሩ አንድነቶች እና ልዩነቶችን እንዲያደንቁ እና የተለያዩ አመለካከቶችን እንዲያከብሩ ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል። "*

- VEYLDF, 2016, pg. 18

ልጅዎ በጨዋታ ላይ እያሉ፣ በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ባህሪያትን እንዲማሩ የሚረዷቸውን ህጎች ይደራደራሉ። ለምሳሌ፣ ልጆች በዥዋዥዌ ላይ ተራቸውን ለመጠበቅ ህግ ሊያወጡ ይችላሉ። ልጆች የሁሉም ሰው ደህንነት እንዲጠበቅ፣ የመሳሪያ እንክብካቤ እንዲሁም ፍትሃዊነት እና ትክክለኛነት ለመደገፍ የሚረዱ ህጎችን ማውጣት ላይ እንዲሳተፉ መፍቀድ የአስተሳሰብ እና ችግር አፈታት ክህሎቶቻቸውን ያግዛሉ እንዲሁም የግንኙነት እና ማህበራዊ እንዲሁም የቁጥር እና የጽሁፍ ክህሎታቸው መዳበርን ይደግፋሉ።

በጨዋታቸው፣ ልጆች በነበራቸው እውቀት እና ሃሳቦች ላይ አዲስ እና አስደሳች በሆኑ መንገዶች መገንባት ይችላሉ።

ልጆች አንዳንድ እንቅሰቃሴዎችን አሁንም አሁንም ሊደጋግሙ ይችላሉ፣ ሃላፊነትን መውሰድ እና መማር እንዲሁም ክህሎቶችን መለማመድ፣ ለምሳሌ፦

- በራሳቸው ወደ ከፍታ ቦታ መውጣት
- የጂግ-ሳው እንቆቅልሽን አጠናቆ ማወቅ
- የራሳቸውን ልብስ ወይም የስእል ልብስ(አርት እስሞክ) መልበስ
- በጠባብ ጨረር ላይ ማመጣጠን
- በራሳቸው መቀሶችን መጠቀም
- መዝለል
- በዥዋዥዌ ላይ ራሳቸውን መግፋት።

እነዚህ ትንንሽ ወይም ትልልቅ ስኬቶች ለልጆች፣ ለቤተሰቦቻቸው እና ትምህርታቸውን ለሚደግፉ አስተማሪዎች የሚሰጡ ሽልማቶች ናቸው።

ጨዋታ፣ ለልጆች የማክበር፣ የማሳካት፣ የማለፍ፣ ስህተት የመስራት፣ የልምምድ፣ አዲስ መረጃዎችን ወይም ክህሎቶችን የመሞከር፣ አስተያየት የመፍጠር እና አዳዲስ ክህሎቶችን እና እውቀትን አጠናቀው የሚያውቁበትን እድሎች ይሰጣቸዋል።

ጨዋታ ልጅዎ የሚማርበት/የሚትማርበት መንገድ ነው።

**ዋቢዎች**

የትምህርት እና ስልጠና ክፍል፣ 2016። *የቪክቶሪያ የቅድመ አመታት የትምህርት እና ልማት ማዕቀፍ (Victorian Early Years Learning and Development Framework)*።